ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት

Tourism Training Institute

ቅጽ 5 ቁጥር 6

መስከረም 2015 ዓ.ም

# የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ለ54ኛ ጊዜ በቱሪዝምና በሆቴል ዘርፍ 296 ሰልጣኞችን አስመረቀ።

የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ለ54ኛ ጊዜ በቱሪዝምና በሆቴል ሥልጠና ዘርፎች 296 ሰልጣኞችን ያስመረቀ ሲሆን ከተመራቂዎቹ 106 የሚሆኑት ወንዶች ናቸው።

የምረቃ ፕሮግራሙን በንግግር የከፈቱት አቶ ጌታቸው ነጋሽ እንደ ተገናገሩት የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና በዓለም አቀፍ ደረጃ እያደገና በመንግስታት ደረጃ ከፍተኛ ትኩረት እያገኘ የመጣ የልማት መሳሪያ መሆኑ በሁሉም ዘንድ ስምምነት ላይ የተደረሰ መሆኑን ጠቁመው የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩትም የአገራችንን የቱሪዝምና ሆስፒታሊቲ እንዱስትሪ ይበልጥ በማስፋት ዜጎችን ከዘርፉ ተጠቃሚ ለማድረግ በክህሎት የዳበረ ስልጠና በስፋት ለመስጠት በትኩረት እየሰራ እንደሚገኝ ጠቅሰዋል።

የክብር እንግዳ የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር አማካሪ ሚኒስተር ዴኤታ ወ/ሮ ነቢሃ መሀመድ በበኩላቸው የቱሪዝም ዘርፉ በርካታ በዘርፉ የሰለጠኑ ባለሙያዎችን የሚፈልግና አገሪቱ ካላት ተፈጥሯዊና ታሪካዊ የቱሪስት መስህብ አንፃር ገና ብቁ ዜጎችን ማፍራት ጠበቅብን መሆኑን አስገንዝበው ለዛሬዎቹ ተመራቂዎች እንኳን ደስ አላችሁ የሚል መልዕክት አስተላልፈዋል።

በመጨረሻም በኢንስቲትዩቱ ከ25 ዓመት በላይ ያገለገሉ መምህራን እውቅና ተሰጥቷቸዋል።










በኮሚኒኬሽን ጉዳዮች የተዘጋጀ

## የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር እና ተጠሪ ተቋማቱ በእንጦጦ ፓርክ

ቱ.ማ.ኢ

መስከረም 8/2015ዓ.ም

የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር እና የተጠሪ ተቋማት አመራርና ሠራተኞች በጋራ የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር ማጠቃለያ እንዲሁም በፓርኩ የተለያዩ ቦታዎች ጉብኝት አካሄዱ ።

የእንጦጦ ፓርክ ካለው ተፈጥሯዊ የአየር ጸባይ እና መልክ ዓምድር ባሻገር በሰው ሰራሽ ውበት በማጌጡ ጥሩ የእረፍት ጊዜ ማሳለፊያ ሆኗል።

እሁድን በእንጦጦ ፓርክ ማሳለፍ ለአዕምሮና ለአካል ጤናም ያለው ፋይዳ ጉልህ ነው። ይህ ሥፍራ ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ይዘቱን በጠበቀ መልኩ ለትውልድ እንዲተላለፍ ለማድረግ አካባቢውን አረንጓዴ የማልበስ ሥራ በተለያዩ ተቋማት እየተከናወነ ይገኛል።

የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት አመራርና ሠራተኞችም ሚኒስትር መስሪያ ቤቱ ባዘጋጀው የችግኝ ተከላ መርሃ ግብር ተሳትፎ አድርገዋል።









## "እናመሰግናለን"

ጳጉሜ 4/2014ዓ.ም

"አካባቢያችሁን ጽዱ ስለምታደርጉ፣ለእንግዶቻችን ደስታ ስለምትፈጥሩ እናመሰግናለን "ክብርት ሙፈሪያት ካሚል።

በማለዳው እንጦጦ ፓርክ የተገኙ ሚኒስትሮችና የተቋማት ኃላፊዎችን በመወከል ክብርት ሙፈሪያት ካሚል አካባቢያችሁን ጽዱ ስለምታደርጉ፣ ለእንግዶቻችን ደስታ ስለምትፈጥሩ እናመሰግናለን ብለዋል።

በከተማችን አናት የሚገኘው እንጦጦ የመዝናኛ ፓርክ ወደ ፓርኩ ለሚመጡ እንግዶች አካባቢውን ንጹህ ለማድረግ ጧትና ማታ በማጽዳት ረጅም የሆነ የእግር ጉዞ በማድረግ ለሚከፍሉት ዋጋ ሁላችንም ምስጋናችንን እንናቀርባለን ።

# የችግኝ ተከላ መርሃግብር  በቱሪስት መዳረሻ ሥፍራዎች

ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት የችግኝ ተከላ ፕሮግራም በተለያዩ ክልሎች የቱሪስት መዳረሻዎች ተተክለዋል፡፡



የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ሀገራዊ አጀንዳ ከራሱ ተልዕኮ ጋር በማጣጣም አረንጓዴ የማልበስ መርሃ ግብርን በአዲስ አበባ እንጦጦ ፓርክ፣ በእንጦጦ ፖሊቴክኒክ፣ በአማራ ክልል በደብረብርሃን ከተማ፣ በኦሮሚያ ክልል ደብረ ሊባኖስ ፖርቹጊስ ድልድይ እና በደቡብ ክልል ጢያ ትክል ድንጋይ አካባቢ በድምሩ 12431 ችግኞችን በኢንስቲትዩቱ ሰራተኞችና ሰልጣኞች እንዲሁም በገነት ሆቴል ሰራተኞች እንዲተከሉ አድርጓል፡፡

በፕሮግራሙ መክፈቻ የተቋሙ ም/ዋና ዳይሬክተር አቶ ገዛኸኝ አባተ እንደተናገሩት ተቋማችን የቱሪዝም ማሰልጠኛ እንደመሆኑ በሀገሪቱ ባሉ በተመረጡ የቱሪስት መዳረሻ ሥፍራዎች ላለፉት ሶስት ዓመታት ችግኞችን ተክለናል፣ አሁንም እንተክላለን የተከልነውንም እንከባከባለን ብለዋል፡፡



ሀገር በቀል የሆኑ እና ለአካባቢ ጥበቃ የሚያገለግሉ ከሁለት ሺህ በላይ ችግኞች በደብረብርሃን በበሬሳ ወንዝ አካባቢ የከተማው የመጀመሪያው የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ጣቢያ የነበረበት ሥፍራ ችግኞቹ ተተክለዋል፡፡

ቦታው ከታሪካዊነቱና ከመልክዓ ምድር አቀማመጡ አንፃር የቱሪስት መዳረሻ ሥፍራ ለማድረግ በከተማ አስተዳደሩ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ እየተሰራ እንደሆነ አቶ አክሊለ ጌታቸው የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ ባለሙያ ተናግረዋል፡፡

በተያያዘም ቦታው ካለው ምቹነት እና ታሪካዊነት አንፃር ለከተማው ወጣቶች የሥራ ዕድል መፍጠር የሚያስችሉ ሥራዎችን ለመሥራት ከከተማ አስተዳደሩ፣ ከሥራና ክህሎት ሚኒስቴር እንዲሁም ከኢንስቲትዩቱ ጋር መሥራት ስለሚቻልበት ሁኔታ አመራሮቹ መክረዋል፡፡ ሌላዉ አዲስ አበባ ቴክኒክና ሙያ ግቢ ውስጥ ነበር፡፡ ተቋማት በጋራ በዚህ መርሃ ግብር መገናኘታቸው በቀጣይ ለሚኖራቸው የሥራ ግንኙነት መልካም መሆኑን የኢንስቲትዩቱ የአመራርና አስተዳደር ዘርፍ ም/ዋና ዳይሬክተር እና የዋና ዳይሬክተሩ ተወካይ አቶ ገዛኸኝ አባተ ተናግረዋል፡፡



የፖሊ ቴክኒክ ኮሌጁ ዲን አቶ ተሾመ ፈይሳ በበኩላቸው እነዚህ ሁለት አንጋፋ ተቋማት በዚህ ለትውልድ የሚሻገር ተግባር ላይ መገናኘታቸው በቀጣይ በጋራ ለሚኖሩ ዘርፈ ብዙ ተግባራት ፈር ቀዳጅ መሆኑን አንስተዋል፡፡

ከ1500 በላይ ችግኞች እና ጉድጓዶች በፖሊ ቴክኒኩ ኮሌጅ የተዘጋጀ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ የቡና ፣የአቦካዶና የማንጎ እንዲሁም አገር በቀል ዛፎች ጽድ እና ዝግባ ችግኞች ተተክለዋል፡፡

በቱሪስት መዳረሻ ሥፍራዎች የጀመረውን የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር ቀጥሎ በእንጦጦ ፓርክ የኢንስቲትዩቱ ፣ የገነት ሆቴል ሰራተኞች እና ሰልጣኞች 2250 ችግኞችን ተክለዋል ፡፡







## ጳጉሜን በመደመር መርሃ ግብርን በማስመልከት ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ለ50 አቅመ ደካሞች የበዓል ማክበሪያ ድጋፍ አደረገ።

ቱ ማ ኢ

ጳጉሜ 3/2014 ዓ ም

የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩትና ገነት ሆቴል በጋራ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ11 ለሚገኙ ለ50 አቅመ ደካማ ቤተሰቦች ለበዓል ማክበሪያ የሚሆኑ አምስት ሊትር ዘይት ፣ አስራ አምስት ኪሎ ፍርኖ ዱቄት ፣አንድ ዶሮና አስር እንቁላል በአጠቃላይ ግምቱ 200 ሺ ህ ብር የሚሆን የምግብ ቁሳ ቁስ ድጋፍ ተደረገላቸው።

የተቋማችን ዋና ዳሬክተር አቶ ጌታቸው ነጋሽ እንደገለጹት ይህ የበዓል ድጋፍ አሁን ባለው የኑሮ ሁኔታ በቂ ሆኖ ሳይሆን መተሳሰባችንን ለመግለጽ እንደሆነ እንዲታወቅና ለወደፊት ከዚህ በተሻለ ሁኔታ በማህበረሰብ አቀፍ ድጋፍ መዕቀፍ ውስጥ የተለያዩ ድጋፎችን እንደሚሰጡ በተቋሙ ስም ቃል ገብተዋል።

የተቋማችን ምርምርና ማማከር ም/ዋና ዳይሬክተር እና የገነት ሆቴል ሥራ አስኪያጅ አቶ ይታሰብ ስዩም እንደተናገሩት ይህ የማህበረሰብ አቀፍ አገልግሎት ዘላቂነት እንዲኖር ከወረዳ አመራር ጨምሮ ያደረጉት ተሳትፎ በማድነቅ በቀጣይም በተለያዩ ድጋፎች ሆቴሉ ከወረዳው ጎን መሆኑን በመግለጽ ለበዓሉ እንኳን አደረሳችሁ መልክት አስተላልፈዋል፡፤








ነሐሴ

# በደንበኞች አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ ስልጠና ተሰጠ።

30/2014 ዓ.ም

ቱ ማ ኢ

ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ከሀያት ሪጀንሲ ሆቴል እና ከዩናይትድ አረብ ኢሚሬትስ ኤምባሲ ጋር በመተባበር ለመደበኛ ሴት ሰልጣኞች በደንበኛ አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ ለሁለት ቀናት ስልጠና ተሰጠ።

በስልጠናው ማጠቃለያ የተገኙት የተቋሙ ዋና ዳይሬክተር አቶ ጌታቸው ነጋሽ እንደገለፁት ሰልጣኞቻችንን ብቁ ባለሙያ ለማድረግ ከመደበኛ ስልጠና ባሻገር ከአጋር አካላት ጋር በመተባበር የሚሰጡ ሥልጠናዎችን አጠናክሮ መስራት ይጠበቅብናል ብለዋል።

አክለውም ለሰልጣኞቻችን የትብብር ስልጠና በመስጠት ይህንመሰል ሥልጠናም በማመቻቸት አጋርነቱን በተግባር የሚያሳየውን ሀያት ሪጀንሲ ሆቴልን አመስግነዋል።

የተከበሩ መሀመድ አልረሺድ በተባበሩት ዐረብ ኢሚሬትስ የኢትዮጵያና የደቡብ ሱዳን አምባሳደር እና የአፍሪካ ህብረት ተወካይ በስልጠናው ማጠቃለያ ተገኝተው ለሰልጣኞቹ የምስክር ወረቀት ሰጥተዋል።





## የኢንስትቲዩቱ አሰልጣኞች የካይዘን ስልጠና ወሰዱ።

**ቱ .ማ .ኢ.**

ሐምሌ 26/2014 ዓ.ም

ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስትቲዩት ከካይዘን ልህቀት ማዕከል ጋር በመተባበር ለተቋሙ አሰልጣኞች በካይዘን ምንነትና አተገባበር ዙሪያ ስልጠና በገነት ሆቴል እየተሰጣቸው ይገኛል።

ስልጠናውን የሚሰጡት የካይዘን ልህቀት ማዕከል ከፍተኛ ባለሙያዎች አቶ ጀሚል አብደላ ስለ ካይዘን ምንነትና አተገባበር አቶ ሶፎኒያስ ዘለቀ ስለ አምስቱ የስልጠና አይነቶች (5S & Muda) እንደሚሰጡ ተናግረዋል።

አሰልጣኝ ጀሚል እንደገለጹት ካይዘን አሰራራችንን እና አመለካከታችንን በቀጣይነት በማሻሻል ወደ ምንፈልግበት ደረጃ ለመድረስ የሚያግዘን የአመራር ጥበብ እንደሆነና የካይዘን የመጨረሻ ግቡ ጥሩ የሥራ ባህልን መገንባትና ተወዳዳሪነት የሚያሳድግ መሆኑን አሰልጣኙ ገልጸዋል።

በስልጠናው የካይዘን ባህሪያት በስፋት ተገልጿል፤ እነዚህም ዘላቂነት ፣ አሳታፊነት፣ የበርካታና የጥቃቅን ለውጦች ድምር ፣ ያለ ከፍተኛ መዋዕለ- ንዋይ ፍሰት የሚፈልቅ ማሻሻያ እና በሁሉም ቦታ በማንኛውም ዘርፍ የሚተገበር መሆኑን ባለሙያው ተናግረዋል።

ስልጠናው ለሁለት ቀን ተሰጥቷል ።





## የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት አመራርና ሰራተኞች በ2015 በጀት ዓመት የሥራ እንቅስቃሴ እና በወቅታዊ ሀገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ውይይት አደረጉ።

ቱ.ማ.ኢ

2014 ዓ.ም

በውይይቱ መክፈቻ የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር አቶ ጌታቸው ነጋሽ እንደተናገሩት ከሀገሪቱ አምስት የኢኮኖሚ ምሰሶዎች አንዱ የቱሪዝም ዘርፉ በመሆኑ እንደተቋም በዘርፉ ስልጠና በመስጠት ለዜጎች የሥራ ዕድል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ከፍተኛ ኃላፊነት ተጥሎብናል ብለዋል።

በዓለም ላይ ከአስር ሰው አንዱ በቱሪዝም መስክ የሥራ ዕድል የተፈጠሰለት እንደሆነ የዓለም ቱሪዝም ድርጅት የሚያወጣው ሪፖርት ይጠቁማል። ሀገራችንም ካላት ተፈጥሯዊ ፣ባህላዊ እና ታሪካዊ ቅርሶች አንፃር ዜጎችን ተጠቃሚ አለማድረጋችን ሁልጊዜም ቁጭታችን መሆኑን በመረዳት የገበታ ለሀገር ፕሮጀክቶች ፣ የእንጦጦ ፓርክና የሸገር ፕሮጀክቶችም መንግስት ለዘርፉ የሰጠው ትኩረት ማሳያ ናቸው።

በተያያዘም ወቅታዊ ሀገራዊ ጉዳዮች ፣ብሔራዊ የምክክር ኮሚሽኑ እና የኑሮ ውድነቱንና ዓለማቀፋዊ ሁኔታ ዳሰሳ የውይይት መነሻ ሰነድ በተቋሙ ም/ዋና ዳይሬክተር አቶ ገዛኸኝ አባተ ቀርቦ በሠራተኛው ውይይት ተደርጓል።

ሰራተኞችም በወቅታዊ ሁኔታ ላይ መወያየታችን ተገቢ ነው ሁላችንም ለሀገራችን የሰላም ግንባታ፣ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በአንድነት ሆነን በዘርፉ ጥራት ያለው የሰለጠነ የሰው ሀይል በማፍራት ተጠቃሚ ማድረግ ይገባናል ያሉ ሲሆን በተቋም ደረጃም ይሁን እንደመንግስት የህዝብን ደህንነት የመጠበቅ፣ በሰራተኛውንና በህብረተሰቡ ላይ ያንዣበበውን የኑሮ ውድነት ችግር ቅድሚያ በመስጠት ሊፈቱ ይገባል በማለት አስተያዬቶች ተሰጥተዋል።

በመጨረሻም የተነሱት ሀሳቦችና የተሰጡት አስተያዬቶች ተገቢ መሆናቸውን፣ ችግሮቹንም ሆነ መንግስትና ህዝብ ከኢንስቲትዩቱ የሚጠብቁትን ለመተግበር ሁላችንም በጋራ መስራት እንደሚጠበቅብን በአመራሮቹ ምላሽና አስተያዬት በመስጠት ተጠናቋል።







## የተቋማት የውስጥ ምዘና ማስተግበሪያ መመሪያ ላይ ውይይት ተደረገ።

ቱ .ማ .ኢ.

ሐምሌ 15/2014 ዓ.ም



የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራስያዊ ሪፐብሊክ የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር የተቋማት የውስጥ ምዘና ማሰተግበሪያ መመሪያ ቁጥር 883/2014 ላይ የኢንስቲትዩቱ አሰልጣኞች ውይይት አድርገዋል።

መመሪያውን ያቀረቡት የተቋሙ የሥልጠናና አቅም ግንባታ ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ሐብታሙ ክብረት ናቸው።

በመመሪያው ከተነሱ ዋና ዋና ጉዳዩች መካከል አንዱ የተቋም የውስጥ ምዘና መሳሪያ ዝግጅት እና ውጤት አሰጣጥ ሂደት ሲሆን ሌላው የተቋማት የውስጥ ስልጠና ደረጃ ምዘና የሰልጣኝ ውጤት አሰጣጥ ነው። በተጨማሪም ከተቋም አስፈጻሚ አካላት ጀምሮ እስከ ሰልጣኝ ተግባርና ኃላፊነት ድረስ ቀርቦ ውይይት ተደርጎበታል።

# የቱሪዝም ዘርፉን በቴክኖሎጂ በመደገፍ ለሀገር ኢኮኖሚ የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዲያበረክት ትኩረት ያስፈልገዋል ተባለ።

ቱ.ማ.ኢ

መስከረም 7/2015 ዓ.ም

ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ከመረጃ መረብ ደህንነት አስተዳደር ጋር በመተባበር የቱሪዝም ዘርፉን በቴክኖሎጂ መደገፍ ስለሚቻልበት ሁኔታ የአስጎብኚ ድርጅቶች፣የቱር ኦፕሬተሮችና የቱር ጋይድ ማህበር አባላት በተገኙበት ውይይት ተካሄደ።

የጉብኝት መርሃግብሩ፤ የመረጃ መረብ ደህንነት አስተዳደር ም/ዋና ዳይሬክተር ወ/ሮ አስቴር ዳዊት እንግዶቹን በተቀበሉበት ወቅት እንደተናገሩት የቱሪዝም ዘርፉን በቴከኖሎጂ በመደገፍ መዳረሻዎችን ማልማት ፣ወደሀገር የሚገቡ ቱሪስቶችን በቂ መረጃ እንዲያገኙ ማድረግ የሚያስችል ስልጠና እንደሚያመቻቹም ገልፀዋል።







# "ውጤታማ የሲቪል ሰርቪስ ሥራ በመሥራት የጠላትን ዓላማ ማክሸፍ ይኖርብናል"

ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ከኢንተርፕርነርሺፕ ልማት ኢንስቲትዩት ጋር በመተባበር የፐብሊክ ኢንተርፕርነር ፕራይቬት ቢዝነስ ላይ ያተኮረ ሥልጠና ባጠናቀቀበት ወቅት የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ክቡር ዶ/ር በከር ሻሌ ተገኝተው እስከ ዛሬ በሄድንበት መንገድ መሄድ ለማንም አይጠቅምም በሥልጠና ታግዞ ዘርፉንና ወቅቱን ያገናዘበ ቴክኖሎጂ መጠቀም ካልቻልን መሻገር አንችልም በማለት መልዕክት አስተላልፈዋል።

ዶ/ር በከር እንደገለጹት ሠራተኛው ይህን ሥልጠና መውሰዱ ሥራን እየፈጠሩ ለየት ያሉ ሃሳቦችን በማምጣት የዕለት ወጪን ከመሸፈን ጀምሮ በትልቅ ደረጃ ሥራ ፈጣሪ መሆን ይቻላል፣ለሰልጣኞችቻችሁም ከመቀጠር ባለፈ በራሳቸው ሥራን መፍጠር እንዲችሉ ማመቻቸት ይጠበቅባችኋል ብለዋል።

የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር አቶ ጌታቸው ነጋሽ በበኩላቸው "ከዚህ የሚበልጥ ተግባር የለንም"በሚል መነሻ ይህን ሥልጠና ወደተግባር መለወጥ እና ውስብስብ የሆኑ አሰራሮችን በማቅለል ሥራን ቀልጣፋ ማድረግ ይጠበቅብናል ካሉ በኋላ ሥልጠናውን የሰጠውን የኢንተርፕርነርሺፕ ልማት ኢንስቲትዩትን አመስግነዋል።

በመጨረሻም በሥልጠናው ንቁ ተሳትፎ ያደረጉ ሰልጣኞች ሽልማት ተበርክቶላቸዋል።

# "እስከ ዛሬ በሄድንበት መንገድ መሄድ ለማንም አይጠቅምም"

## ዶ/ር በከር ሻሌ በሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ



ነሀሴ 28/2014ዓ.ም

ቱማኢ

የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት በወቅታዊ ሀገራዊ ጉዳይ ውይይት አደረጉ።

ክቡር ዶ/ር በከር ሻሌ የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ እና የተቋሙ ከፍተኛ አመራሮችና ሠራተኞች በወቅታዊ ሀገራዊ ጉዳይ ላይ ውይይት ባደረጉበት ወቅት አሸባሪው ቡድን የሰላምን አማራጭ ሁሉ ወደኋላ በማለት ለሦስተኛ ጊዜ ጦርነት መክፈቱን በመጥቀስ ሁሉም በተሰማራበት የሙያ መስክ በተለይም የሲቪል ሰርቪስ ሠራተኛው ጠንክሮ በመስራት የጠላትን ዓላማ ማክሸፍ ይኖርበታል ብለዋል።

የተቋሙ ም/ዋና ዳይሬክተር አቶ ገዛኸኝ አባተ የውይይት መነሻ ሰነድ አቅርበው ውይይት ተካሂዶበታል።

በመጨረሻም ሠራተኛው መንግስት በሚፈልገው ጥሪ ሁሉ እንደዚህ ቀደሙ ተሳታፊ እንደሚሆን የገለጸ ሲሆን እንደተቋምም ደጀንነታችንን በማሳየት ግንባር ቀደም ነን ብለዋል።







# የተቋሙ አዳዲስ አመራሮች ከሰራተኛው ጋር ትውውቅ አደረጉ፡፡

ቱ.ማ.ኢ

ሐምሌ 6/2014 ዓ.ም

"ተቋሙን ከፍ ወዳለ ደረጃ ለማሳደግ ከሁላችን የሚጠበቅ ውጤት አለ" አቶ ጌታቸው ነጋሽ

የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር አቶ ጌታቸው ነጋሽ እና የተቋሙ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች አቶ ሀብታሙ ክብረት፣ አቶ ገዛኸኝ አባተ እና አቶ ይታሰብ ስዩም ከሰራተኞች ጋር ትውውቅ አደረጉ፡፡

ዋና ዳይሬክተሩ በመግቢያቸው እዚህ የተመደብነው አዳዲስ እና ነባር አመራሮች ከእናንተ ጋር በመሆን ለዘርፉ መንግስት የሰጠውን ትኩረት መሰረት ያደረገ ተቋሙን ከፍ ወዳለ ደረጃ ማሳደግ የሚጠበቅብን ውጤት አለ ብለዋል፡፡ ተቋማችን በቱሪዝምና ሆስፒታሊቲው ዘርፍ የልህቀት ማዕከል ሆኖ መቀጠል እንዲችል በትኩረት መሥራት ይጠበቅብናል በማለት ሀሳባቸውን ገልጸዋል፡፡

የተቋሙ ነባር ም/ዋና ዳይሬክተር አቶ ገዛኸኝ አባተ የ2014 ዓ.ም ዕቅድ ሪፖርት እና የ2015 በጀት ዓመት የትኩረት አቅጣጫዎች ላይ ገለፃ አድርገዋል፡፡

በመጨረሻም ከመምህራን እና ከሰራተኞች የቀረቡ ጥያቄዎችና አስተያየቶችን ሁሉም አመራሮች ከተነሱ ነጥቦች አኳያ ምላሽ ሰጥተውባቸዋል፡፡

ተቋሙ ላለፉት 10 ዓመታት ከኢንስቲትዩት ወደ ማዕከል በመውረዱ ምክንያት የእድሜውን ያህል ለዘርፉ ማበርከት ያለበትን የሰለጠነ የሰው ሃይል ማቅረብ እንዳይችል ተግዳሮት እንደነበረበት በተለያዩ አጋጣሚዎች ማንሳታችን የሚታወስ ሲሆን በዚህ ዓመት ወደ ኢንስቲትዩት አድጎ ቀድሞ ከነበረው አቅም በተሻለ አመራር ከሀገራችን አልፎ ከምስራቅ አፍሪካ ካሉ አቻ ተቋማት ጋር ተወዳዳሪ መሆን የሚያስችለውን የበጀትና የሰው ሃይል ድጋፍ ማድረጉ በእጅጉ የሚያበረታታ ነው፡፡






## የአሰራር ሥርዓት ማዕቀፍ እየተዘጋጀ ነው

ቱ.ማ.ኢ

መስከረም 12/2015ዓ.ም

ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት በቱሪዝምና ሆስፒታሊቲ ሥልጠና ዘርፍ የልህቀት ማዕከል በመሆን ለዘርፉ ጉልህ አስተዋጽኦ ሊያበረክት የሚችል ተቋም ሆኖ እንዲቀጥል የሥራ ባህልን መገንባትና የሥራ ፍሰትን በጠበቀ መልኩ የአሰራር ሥርዓት ሊኖረን ይገባል ሲሉ አቶ ሀብታሙ ክብረት የስልጠናና አቅም ግንባታ ዘርፍ ም/ዋና ዳይሬክተር ተናገሩ።

ስለሆነም በሁሉም የስልጠና ዘርፎች እና ሬጅስትራር የአሰራር ማዕቀፍ እየሰራን እንገኛለን ብለዋል፤ በተለይም የማታና አጫጭር ሥልጠና ፣ የቋንቋ ሥልጠና ዘርፎች (እንግሊዝኛ እና ፈረንሳይኛ)፣ በአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት መሰረት በአሰልጣኞቻችን እና ከሥራና ክህሎት ሚኒስቴር በመጡ ባለሙያ እገዛ እየተዘጋጀ ይገኛል።

የአሰራር ስርዓት መዘጋጀቱ የሥራ ባህልን ከማጠናከሩ ባሻገር ሥራን በአግባቡ መፈጸም፣ ተጠያቂነትን ለማስፈን እና በሥራው ፣ በሰራተኛው ፣ በአሰልጣኝና በሰልጣኝ መካከል ጤናማ የሆነ ግንኙነትን የሚፈጥር መሆኑን ይህን የአሰራር ሥርዓት የመያዘጋጁ ባለሙያዎች ገልፀዋል።

ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ላለፉት 54 ዓመታት በቱሪዝምና ሆስፒታሊቲ ዘርፍ ሥልጠና በመስጠት የቆየ አንጋፋ ተቋም ሲሆን አሁን እየተሰሩ ያሉ የአሰራር ማዕቀፎች አንዳንዶቹ ቀድሞ ተቋሙ ኢንስቲትዩት በነበረት ወቅት ሲገለገልበት የነበረ ሲሆን መልሶ ለመጠቀም እና ዘመኑን በሚመጥን መልኩ በአዲስ መልክ የሚዘጋጁ ናቸው።

ከአዘጋጆቹ በከፊል







# "አዲስ እሳቤ ለቱሪዝም"



የዓለም ቱሪዝም ቀን በሀገራችን ለ35ኛ ጊዜ በአሶሳ ከተማ ተከበረ።
ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ከቤንሻንጉል ጉምዝ ክልልና ከቱሪዝም ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ኬክ ዝግጅትና ኮንፈረንስ ላይ ተሳትፎ ያደረገ ሲሆን
ከበዓሉ ቀደም ብሎ በከተማው የሚገኙ ሆቴሎች ለበዓል የሚመጡ እንግዶችን ማስተናገድ የሚያስችል ሥልጠናና የማማከር አገልግሎት በተቋሙ ባለሙያዎች ተሰጥቷል። በተጨማሪም የክልሉን ባህላዊ ምግብ በሜኑ መልክ ለማዘጋጀት የሚያስችል ሥራ በተቋሙ ባለሙያዎች ተጀምሯል።

